

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

## የቀረበ የ2017 በጀት ዓመት የበጀት መግለጫ

አህመድ ሽዴ

የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር

ሰኔ 04/2016 ዓ.ም.

# Budget Speech

## ክቡር አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት

ዛሬ በዚህ ም/ቤት የተገኘሁት በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በተደነገገው መሠረት በሚኒስትሮች ም/ቤት ተደግፎ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ የቀረበውን የ2017 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ረቂቅ በጀት አስመልክቶ ለተከበረው ም/ቤት ዝርዝር መግለጫ ለማቅርብ ነው።

ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ የገጠሙንን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማነቆዎችን እልባት ለመስጠት መጠነ ሰፊ ሪፎርሞችን ተግባራዊ ተደርገዋል። በዚህም በአፍሪካ ከሚገኙ ትላልቅ ኢኮኖሚዎች አንዱ የሆነውን የሀገራችንን ኢኮኖሚ አስተማማኝ የዕድገት ሃዲዱን ይዞ እንዲቀጥል ለማስቻል ሁለተኛው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተቀርጾ ከሀገሪቱ የመካከለኛ ዘመን የልማትና ኢንቨስትመንት ዕቅድ ጋር በማስተሳሰር ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል።

ይህ የ2017 የፌዴራል መንግስት በጀትም እስካሁን ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉትንና በቀጣይ ለመተግበር የታቀዱትን የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ተግባራዊነት እና ውጤታማነት በማጠናከር የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለማስቀጠል እና የተዛባውን የማክሮ ኢኮኖሚው ሚዛን ለማስተካከል በሚያግዝ መልኩ የተዘጋጀ ነው።

## ክቡር አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት

በመጀመሪያው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ በርካታ ግቦችን እና ውጤቶችን ማሳካት ተችሏል። በሌላ መልኩም ውስጣዊና ውጫዊ በሆኑ ተደራራቢ ተግዳሮቶች ምክንያት ያላሳካናቸው ግቦች መኖራቸውም የሚታወቅ ነው። ያሉንን የውስጥ አቅሞች አሟጠን ለመጠቀም በተደረገው ከፍተኛ የመንግስት ጥረት አካታች፣ ጥራት ያለውና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስቀጠል ተችሏል። የማሻሻያዎቹ ተግባራዊነት እና ውጤታማነት ኢኮኖሚያችን ላሳየው አይበገሬነት (resilience) የነበረው አበርክቶ ከፍተኛ ነው።

ኢትዮጵያ ስኬት እያስመዘገበች መጓዝ የምትችል ሀገር በመሆኗ፣ ባለፉት ዓመታት የገጠሙንን ተደራራቢ ተግዳሮቶች ተቋቁመን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ በቅተናል። በዚህም የተነሳ ከ2012-2015 ባሉት የማሻሻያው ትግበራ ዓመታት የ6.5 በመቶ አማካይ የዕድገት ምጣኔ ተመዝግቧል። በተለይም በ2015 በጀት ዓመት የተሻለ ዕድገት የተመዘገበ ሲሆን፣ የዕድገት

ምጣኔውም 7.2 በመቶ ነው። ይህም ከሰሀራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ከተመዘገበው አማካይ ዕድገት ጋር ሲነጻጸር እጥፍ ነው።

ይህ የኢኮኖሚ ዕድገት የተመገበው በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች በተከናወኑ መጠነ ሰፊ የልማት ሥራዎች የተነሳ ነው። በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች በነዚህ ዓመታት የተመዘገበው አማካይ ዕድገት በቅደም ተከተል 5.6፣ 7.2 እና 6.8 በመቶ ነው። ይህንንም ተከትሎ የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ በ2010 በጀት ዓመት ከነበረበት 882 የአሜሪካን ዶላር በ2015 በጀት ዓመት ወደ 1,549 የአሜሪካን ዶላር ከፍ እንዲል አድርጓል።

በውጭ ንግድ ዘርፉ በኩል የኤክስፖርት ገቢ አፈጻጸም እንዲሻሻል በተደረጉ ጥረቶች ባለፉት ዓመታት ውጤቶች ተመዝግበዋል። የኤክስፖርት ገቢ ከ2012-2014 ባሉት ዓመታት የ15.5 በመቶ አማካይ ዕድገት አስመዝግቧል። እንዲሁም ከኢኮኖሚ ማሻሻያው በተጨማሪ ማነቆ ሆነው የቆዩ አሰራሮችን ለማሻሻል የተደረጉ ለውጦች እና በዲፕሎማሲውና በውጭ ግንኙነት ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ አዎንታዊ አስተዋጽኦ አድርገዋል። የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትም በነዚህ ዓመታት መሻሻል አሳይቷል።

የፋይናንስ ዘርፉን ከማሳደግ አንጻርም ባለፉት ዓመታት ሰፋፊ የማሻሻያ ሥራዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። የባንኮች የተቀማጭ ገንዘብ እና የብድር አቅርቦት ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል፣ እንዲሁም የባንክ ቅርንጫፎች በመስፋፋታቸው እና በዲጂታል አገልግሎት ከፍተኛ ዕድገት የተነሳ የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት መሻሻል እንዲያሳይ ከፍተኛ ዕገዛ አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ፣ የፋይናንስ አገልግሎቱን አካታች እና ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያን ለማቋቋምም አመርቂ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን፣ በቅርቡ የሰነድ ገበያ ማካሄድ ይጀምራል።

በፊስካል ዘርፉም እንዲሁ የመንግስትን ገቢ አሰባሰብ ለማሳደግ የሚያስችሉ በርካታ የታክስ ፖሊሲ እና የታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎች ተግባራዊ ሆነዋል። በዚህ ትግበራ ምክንያትም ባለፉት ዓመታት የመንግስት ገቢ ዕድገት አሳይቷል። በተለይም የታክስ ገቢ ከ2012-2015 ባሉት ዓመታት ውስጥ የ22.4 በመቶ ዕድገት አለው። ሆኖም ግን የታክስ ገቢ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ ለማሳደግ በቀጣይ ጠንካራ ሥራ መስራት ይጠበቅብናል።

በሌላ በኩል የመንግስት ወጪ ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው አምራች ዘርፎች፣ መሠረተ ልማቶች ማስፋፊያና ሰብዓዊ ልማትን ለማሳደግ የሚረዱ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም እንዲውል ከፍተኛ ጥረት

ተደርጓል፡፡ ሀብትን በቁጠባ በመጠቀም ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የሚያስችሉ የመንግስት የፋይናንስ ሥርዓት ማሻሻያዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

በሌላ በኩል በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚታዩ ዘርፈ ብዙ መዋቅራዊ ማነቆዎችን ለመፍታት ረጅም ርቀት በመሄድ የተፋጠነ የልማት ሥራዎች በማካሄድ ጉልህ አቅሞች መገንባት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የመንግስት የልማት ድርጅቶች የአመራር አቅማቸውን ለመገንባት፣ ቅልጥፍናቸውን ለመጨመርና እና ትርፋማነታቸውን ለማሳደግ የሚያስችሉ በርካታ ማሻሻያዎች ተከናውነዋል፡፡ እንዲሁም የመንግስት ልማት ድርጅቶችን በዘመናዊ መንገድ ለማስተዳደር የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ተቋቁሞ በልማት ድርጅቶቹ የአመራርና የኢንቨስትመንት ውሳኔን ለማሻሻል የሚያስችሉ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን፣ የአመራርና ውጤታማነትን ለማሻሻልና ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን ከውጭ አጋሮች ጋር በጋራ ለማካሄድ ጠንካራ የሪፎርም ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግን ለማጠናከር ማሻሻያው ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ማሻሻያዎች ተግባራዊ በመደረጋቸውም ከዚህ ቀደም በኪሳራ ውስጥ የነበሩ ድርጅቶች ትርፋማ መሆን ችለዋል፡፡

## ክቡር አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት

ባለፉት ዓመታት በርካታ የልማት ስኬቶችን ማረጋገጥ መቻሉ እሙን ነው፡፡ በተነጻጻሪ ደግሞ በገጠሙን ተደራራቢና ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች ምክንያት በኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራው ያልቀረፍናቸው ተግዳሮቶችና ማሻሻያቸውንም በተሟላ ሁኔታ ያልተገበርንበት ሁኔታ አለ፡፡

ከእነዚህም መካከል አንዱና ዋናው የዋጋ ንረት ነው፡፡ በቅርብ ወራት የዋጋ ዕድገት መጠነኛ ቅናሽ እያሳየ የመጣ ቢሆንም ወደ አንድ አሃዝ ዕድገት እንዲወርድ ማድረግ አልተቻለም፡፡ ምንም እንኳን መንግስት አስፈላጊ የሆኑ የገንዘብ እና የፊስካል ፖሊሲ እርምጃዎችን እየወሰደ ቢሆንም የዋጋ ንረትን ወደ ሚፈለገው ደረጃ ማውረድ አልተቻለም፡፡ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት በአቅርቦት ረገድ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ተገቢ ነው ብለን እናምናለን፡፡ በአንጻሩ ረዥም የአቅርቦት ሰንሰለት መኖር፣ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ውስንነት፣ የነዳጅ ዘይትን ጨምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታየው የሸቀጦች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ መናር እንዲሁም በቀይ ባህር የንግድ መተላለፊያ መስመር ላይ የሚታዩ እክሎች የዋጋ ንረቱን ለመቆጣጠር የሚደረገውን ጥረት እየተገዳደሩ ይገኛሉ፡፡ በመዋቅራዊ እና መፍትሔያቸው በመንግስት እጅ ባልሆኑ ምክንያቶች የሚከሰተውን የዋጋ ጭማሪ ለማስቆም አሁንም ጊዜና ብርቱ ትግል የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ ለፊስካል ጉድለት መሸፈኛ የሚወሰዱ

ብድሮችን በመገደብም ሆነ ብድሮቹ ሲወሰዱ የዋጋ ንረትን የማያስከትሉ የብድር ዓይነቶችን ጥቅም ላይ በማዋል ከዚህ ምንጭ ሊመጣ የሚችለውን የዋጋ ንረት መገደብ በኢኮኖሚ ማሻሻያው የተያዘ አንዱና ትልቁ እርምጃ ነው፡፡ ለዚህም የገንዘብ ፖሊሲውን ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ማሻሻያዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡

የውጭ ክፍያ ሚዛን ጫና እና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ሌላው መቀረፍ የሚገባው የማክሮ ኢኮኖሚ ተግዳሮት ነው፡፡ የኤክስፖርትን ገቢ ለመጨመር የኤክስፖርት መዳረሻ ገበያዎችን በማስፋት ወደ ውጭ የምንልካቸውን የዕቃዎች ዓይነትና መጠን እንዲሁም ጥራት ለማሳደግ በዘርፉ የሚታዩ በርካታ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡ በዘርፉ የሚታዩ በርካታ ማነቆዎችን መፍታት ደግሞ ሌላኛው መፍትሔ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ሥርዓታችንን ለህገ ወጥነት እንዲጋለጥ የሚያደርጉትን ጉዳዮች በመለየት ለዚህ የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ ይታመናል፡፡ ይህም የሚወሰደው መፍትሔ አሁን የሚታየውን የውጭ ክፍያ ሚዛን ጫና እና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ችግር ለመፍታት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

ሌላኛው የፊስካል ዘርፉን የሚመለከቱ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ ባለፉት ዓመታት ከታክስ ምንጭ የተሰበሰበው ገቢ በኢኮኖሚ ውስጥ ካለው አቅም አንጻር ዝቅተኛ በመሆኑ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ጋር ያለው ጥመርታ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ እየተሰበሰበ ያለው ገቢም የመንግስትን የልማት ወጪ ፍላጎት በተሟላ ለመሸፈን የሚያስችል አይደለም፡፡ ይህም መንግስት ለማህበረሰቡ ቃል የገባውን የልማት ሥራዎች በሚፈለገው ደረጃ እንዳያካሄድ ከፍተኛ እንቅፋት ሆኗል፡፡ የወጪ ፍላጎቱ በዚሁ ልክ እየጨመረ የመጣ ከመምጣቱም ባሻገር፣ ባለፉት ዓመታት የተከሰቱትን አስገዳጅና መሠረታዊ የመንግስት ወጪ ፍላጎቶች የግድ መሸፈን አስፈላጊ ሆኗል፡፡ ይህም የመንግስት ወጪ ከፍተኛ የአገር ውስጥ ብድር በመውሰድ እንዲሸፈን በማስገደዱ የፊስካል ቁመናችን ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ስለሆነም፣ ይህንን የፊስካል ቁመናችንን ወደ ጤናማ ሁኔታ ለመመለስና ያለብንን የብድር ጫና ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት እና የልማት ወጪ ፍላጎቶቻችንን በራሳችን ገቢ ለመሸፈን በኢኮኖሚ ውስጥ የሚመነጨውን የታክስ ገቢ አቅም አሟጦ መጠቀም ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህንንም ተግዳሮት መፍታት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ከፊስካል ጋር የተያያዘው ሌላው ተግዳሮት የውጭ ሀገር ዕዳ ጫና ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት ዕዳችንን በአግባቡና በወቅቱ በመክፈላችንና ተጨማሪ የንግድ ብድር ባለመውሰዳችን የውጭ ዕዳ ክምችት እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ነገር ግን የውጭ ዕዳ የስጋት ደረጃ አሁንም በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

ይህንንም የውጭ ዕዳ ስጋት መቀነስ የፊስካል ቁመናችንን ለማሻሻል እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑም በተጨማሪ ልማታችንን ለማፋጠን የሚቀረጹ አዋጭ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚስችል የፋይናንስ አቅም ለማግኘት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ከአበዳሪዎች ጋር የተጀመሩ የዕዳ ሽግሽግና የዕዳ ማቃለያ ድርድሮችን ውጤታማ በማድረግ ይህንን ማሳካት የግድ አስፈላጊ ነው፡፡

## ክቡር አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት

እነዚህን ያላሳካናቸውንና አዳዲስ የተጣሉ ግቦችን ለማሳካት መንግስት የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሁለተኛ ምዕራፍ ፕሮግራም በማዘጋጀት ከያዝነው በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ማድረግ ጀምሯል፡፡ ይህም የማሻሻያ ፕሮግራም ሀገሪቱ የገጠሟትን ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች እና የሚታዩትን ስር የሰደዱ መዋቅራዊ ችግሮችን በመቅረፍ የሀገሪቱን ብልጽግና ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው እሙን ነው፡፡ በተለይም የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባቱን በማስተካከል ለውጦችን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማሻሻያዎች ተግባራዊ የሚሆኑበት ነው፡፡

የኢኮኖሚ ማሻሻያው በአራት ዋና ዋና ምሰሶዎች ላይ የተመሠረተ ሲሆን፤ እነዚህም የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን ማረጋገጥ፣ የኢንስትመንትና የንግድ ከባቢን ማሻሻል፣ የዘርፎችን የማምረት አቅም፣ ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ እና የመንግስትን የመፈጸም አቅም ማጎልበት የሚመለከቱ ማሻሻያዎች ናቸው፡፡

የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያው በዋናነት የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር፣ የውጭ ኢኮኖሚ ዘርፍና ክፍያ ሚዛንን በማስተካከል እና የውጭ ምንዛሬ እጥረትን በመቅረፍ፣ እንዲሁም ጤናማ የዕዳ ሁኔታን በማስፈን እና የፊስካል ዘርፉን ዘላቂነት (fiscal sustainability) በማረጋገጥ ዘላቂና አካታች የኢኮኖሚ ዕድገትን በማስመዝገብ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በዚህ ማሻሻያ ስር ተግባራዊ ለማድረግ ከታቀዱት ዋና ዋና የማሻሻያ እርምጃዎች መካከል የታክስ ገቢን ለማሳደግ፣ የመንግስትን ወጪና ድጎማ ስርዓት ወጤታማነት ለማጎልበት፣ የመንግስት ኢንቨስትመንትና የልማት ድርጅቶችን ውጤታማነት ቅልጥፍና ለማሻሻል፣ የሀገሪቱን የዕዳ የመሸከም አቅም ለማሳደግና ጤናማ የዕዳ ሁኔታን ለማስፈን፣ የገንዘብ ፖሊሲ ማዕቀፍን ለማዘመን፣ የሀገር ውስጥ ቁጠባና የኢንቨስትመንት ፋይናንስ ተደራሽነትን ለማስፋት እንዲሁም የውጭ ኢኮኖሚ ከፍያ ሚዛንን እና የውጭ ምንዛሬ አጠቃቀምን ለማሻሻል አስፈላጊ የሆኑ የማሻሻያ እርምጃዎች ይገኙበታል፡፡ እነዚህን እርምጃዎች ተግባራዊ በማድረግም ለውጭ ተፅእኖ ያለንን ተጋላጭነት በመቀነስ የማይበገር እና ዘላቂ የኢኮኖሚ ልማት ማስፈንን ዓላማ ያደረገ የማሻሻያ ፕሮግራም ነው፡፡

ከዚሁ በተጓዳኝ የኢንቨስትመንትና የንግድ ከባቢን ለማሻሻል ተግባራዊ ከሚደረጉ ማሻሻያዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ ለገበያ ውድድር ምቹ መደላድል የሚፈጥሩ ተቋማዊና የቁጥጥር ማዕቀፍ ማበጀት፣ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚያስችል ከባቢ መፍጠር፣ የመሰረተ ልማትና ሎጂስቲክ ልማትና አገልግሎት ማጎልበት እንዲሁም የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ ከሚተገበሩ ማሻሻያዎች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ማሻሻያዎች ሲተገበሩ የሚጠበቁ ውጤቶች አሉ፡፡ በውድድር ላይ የተመሰረተ የሀገር ውስጥ ገበያ ስርዓትን በማጎልበት ምርትና አገልግሎት ያለ እንከን ከአምራቾች ወደ ሸማቾች እንዲደርስ ማስቻል፤ አገራዊ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ፣ የኤክስፖርት ዘርፍ ተወዳዳሪነት መሻሻል፤ ጥራት ያላቸውንና በልዩ ልዩ ዘርፍ የሚሰማሩ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰት መጨመር፤ የአነስተኛ፣ ጥቃቅንና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ምርታማነትና ተወዳዳሪነት መሻሻል፤ እንዲሁም የተጣጣመ የስራ አቅርቦትና ፍላጎት መስፈን ናቸው፡፡

የብዝሀ ዘርፎች የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነትን ለማረጋገጥ የዘርፎችን የማምረት አቅም፣ ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ማሳደግ ሌላኛው የማሻሻያው የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ድህነትን ለመቀነስ፣ የህብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታን ለማሻሻል፣ አካታች ኢኮኖሚ ዕድገትን ለማረጋገጥ፣ ዋጋን ለማረጋጋት እንዲሁም የሀገር ውስጥ ቁጠባ እና ታክስ ገቢን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ በዘርፍ ማሻሻያዎች ደረጃ ትኩረት ከሚደረግባቸው ተግባራት መካከል የግብርናውን ዘርፍ ምርትና የምርታማነት ዕድገትን ማስፋት፣ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪውን የማምረት አቅምን ማሳደግ፣ የማዕድን ኢንዱስትሪን ተወዳዳሪነትና ዕድገት ማጎልበት፣ የግንባታ ኢንዱስትሪውን ቅልጥፍናና ትራንስፎርሜሽን ማሻሻል፣ የቱሪዝም ዘርፉን ለኢኮኖሚ ልማት የሚያበርክተውን አስተዋጽኦ ማስፋት፣ ዘላቂ ልማትንና ብልጽግናን የሚያረጋግጡ የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና ፈጠራዎች ባለቤት መሆን እንዲሁም የማይበገርና አረንጓዴ ኢኮኖሚ ምርታማነትን ማረጋገጥን ያካተተ ነው፡፡

አራተኛው የትኩረት አቅጣጫ የመንግስትን የመፈጸም አቅም ለማጎልበት ተግባራዊ የሚደረጉ ማሻሻያዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውን ጨምሮ ሌሎች ማሻሻያዎችን በተሟላና በብቃት እንዲሁም በተቀመጠው መርሀ ግብር መሠረት ለማስፈጸም መንግስታዊ የማስፈጸም አቅም የጎላ ጠቀሜታ አለው፡፡ በዚህም የተቀላጠፈ ቢሮክራሲ በማስፈን እንዲሁም የመንግስት ተቋማትን አቅም በማጠናከር እና የአሰራር ግልጽነትን በመፍጠር ሙስናንና ብልሹ አሰራሮችን ለመቅረፍ ሚናው የጎላ ነው፡፡ በዚህም ተግባራዊ ከሚደርጉ ማሻሻያዎች መካከል

የመንግስት አስተዳደርና ተቋማዊ ሪፎርም፣ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ሪፎርም፣ ውጤታማ አመራርና የአቅም ግንባታ ሪፎርም እና የሲቪል ሰርቪስ ዲጂታይዜሽን ሪፎርምን የሚያካትቱ ማሻሻያዎች ይገኙባቸዋል።

## ክቡር አፈ ጉባኤ
## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት

እነዚህን የሪፎርም እርምጃዎች በቁርጠኝነትና በውጤታማነት ተግባራዊ በማድረግ ካሉብን ተደራራቢ የኢኮኖሚ ተግዳሮቶች መላቀቅ የሀገራችንን የብልጽግና ጉዞ በአስተማማኝ መሠረት ላይ መጣል ማለት ነው። የእነዚህ ችግሮች መቀረፍ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚን በማረጋገጥ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትን ለመጨመር፣ ኤክስፖርት ገቢን ለማሳደግ፣ ኢንቨስተሮችና አበዳሪዎች በኢኮኖሚያችን ላይ አስተማማኝ እምነት እንዲኖራቸው በማድረግ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና የመበደሪያ ወጪያችን (cost of borrowing) እንዲቀንስ ለማድረግ፣ የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታ እንዲኖር በማስቻል የድህነት ምጣኔን ለመቀነስና የገቢ ክፍፍል ልዩነትን (income inequality) ለማጥበብ የሚረዳ ይሆናል።

በመሆኑም፣ ይህንን ሁለተኛውን የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ የመንግስት ተቋማት፣ የግሉ ዘርፍና ህብረተሰቡ በአጠቃላይ በተቀናጀ መልክ ተግባራዊ በማድረግ አመርቂ ውጤቶች ለማስመዝገብ ጥረቶች የሚደረጉ ይሆናል። የኢኮኖሚ ማሻሻያዎቹ በየግዜው እየተፈተሹ ተግዳሮቶችን ለመፍታት፣ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና የኢኮኖሚ ዕድገቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ተግባራዊ ይደረጋሉ።

## ክቡር አፈ ጉባኤ
## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት

በምክር ቤቱ እንዲጸድቅ አሁን የቀረበው የ2017 የፌዴራል መንግስት ረቂቅ በጀት የተዘጋጀው ይህንን የሁለተኛውን የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መሠረት በማድረግ ነው። ዋና ዓላማውም ጤናማ የፊስካል ሁኔታን ማረጋገጥ ነው። በመሆኑም፣ ረቂቅ በጀቱ የተዘጋጀው ቅድሚያ ትኩረት የሚደረግባቸውን የገቢና የወጪ የፊስካል ፖሊሲ አቅጣጫዎችን፣ ወቅታዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን እና የኢኮኖሚ ማሻሻያውን የትኩረት አቅጣጫ ባገናዘበ መልኩ ነው። ለዚህም በተቻለ አቅም ገቢን በማሳደግ እና የወጪ ሽግሽጎችን ተግባራዊ በማድረግ የበጀት ጉድለቱን ትርጉም ባለው መልኩ እንዲቀንስ በማድረግ የተዘጋጀ ነው። ስለሆነም መንግስት የሚወስደውን ቀጥታ ብድር (direct advance) በተወሰነ ደረጃ ገታ በማድረግ፤ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎን ለማሳደግና ጤናማ የመንግስት ብድር ሁኔታን ለማረጋገጥ የሚያስችል በጀት እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

የመንግስት በጀትን በዘላቂነትና በአስተማማኝነት ተግባራዊ ለማድረግ የመንግስት ገቢ አሰባሰብን ማሳደግ ወሳኝ ነው፡፡ ስለዚህም በኢኮኖሚ ውስጥ ሊመነጭ የሚችለውን የገቢ አቅም አሟጦ ለመጠቀም የሚያስችሉ የታክስ ፖሊሲና የታክስ አስተዳደር ማሻሻያዎች በተጠናከረ መልክ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ ለዚህም እነዚህን ማሻሻያዎችና የትግበራ ስልት ያካተተ የመካከለኛው ዘመን የገቢ ስትራቴጂ (Medium-Term Revenue Strategy-MTRS) ተዘጋጅቷል፡፡ ይህም በሚኒስቴሮች ም/ቤት ጸድቆ ስራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

በዚህ ስትራቴጂ ውስጥ ተካተው በ2017 በጀት ዓመት ተግባራዊ ለማድረግ ከታቀዱ የታክስ ፖሊሲ እርምጃዎች መካከል የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ማሻሻያና የኤክሳይዝ ቴምብር ቀረጥ ሥርዓት ዋናዎቹ ናቸው:: በተለይም የኤክሳይዝ ቴምብር ቀረጥ ሥርዓትን በሥራ ላይ ማዋል የታክስ ስወራንና ማጭበርበርን በመግታት የኤክሳይ ታክስ አዋጅን በውጤታማነት ተግባራዊ በማድረግ ከታክሱ የሚጠበቀውን ገቢ ለመሰብሰብ ወሳኝ ርምጃ ነው፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝግጅቶች እየተጠናቀቁ በመሆናቸው ከበጀት ዓመቱ መጀመሪያ አንስቶ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅም በሚኒስትሮች ም/ቤት ተደግፎ በተከበረው ም/ቤት እንዲጸድቅ መቅረቡ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህም በምክር ቤቱ ፀድቆ ከ2017 በጀት ዓመት መጀመሪያ ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚደረግ ይጠበቃል፡፡ የቀረበው ረቂቅ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ አዋጅ ዝቅተኛ ገቢ ያለው ህብረተሰብ እምብዛም የማይጠቀምባቸውንና ከዚህ በፊት ከታክሱ ነጻ የነበሩ አዳዲስ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግብይት ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲጣልባቸው የሚያደርግ በመሆኑ የአዋጁ ተግባራዊ መደረግ ተጨማሪ ገቢን የሚያስገኝ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም አዲሱ የንብረት ታክስ አዋጅ በሀገር ደረጃ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ከፀደቀ በኋላ በየክልሎቹ እና ከተማ አስተዳደሮቹ ም/ቤቶች ዝርዝር የአፈጻጸም አዋጅ በማውጣት ሥራ ላይ እንደሚውል ይጠበቃል፡፡ ይህም ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት እና የከተማ አስተዳደሮች ጠቀም ያለ ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኝ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል የታክስ አስተዳደሩን ለማሻሻል ትርጉም ያላቸው ለውጦችን ለማምጣት የሚያስችሉ ማሻሻያዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ የታክስ አስተዳደሩን ዘመናዊና ተደራሽ ለማድረግ፣ የአሠራር ግልጸኝነትን ለማስፈን፣ የታክስ ኦዲትን ውጤታማነት ለማጠናከር፣ የታክስ አስተዳደር ሥርዓቱ በዲጂታላይዜሽን እንዲታገዝ የሚያስችሉ በርካታ ማሻሻያዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

ከታክስ ገቢ በተጨማሪ ታክስ ያልሆኑ ገቢዎችና የልማት አጋሮች የውጭ ሀብትም የ2017 በጀትን ፋይናንስ ለማድረግ እንደሚውሉ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በተለይም ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች ከሚመነጩባቸው ሁሉም ተቋማት ሊገኝ የሚችለው ገቢ በገቢ ዕቅድ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ከልማት አጋሮቻችን ሊገኝ የሚችለው ገቢም እንዲሁ በዕቅድ የተያዘ ሲሆን፣ በያዝነውና ባለፉት ዓመታት የተሰበሰበውን ያህል በገቢ ዕቅዱ ለማካተት ተሞክሯል፡፡

በወጪ ረገድ የበጀቱ ትኩረት ከሚኖረው የገቢ አቅም ጋር የተጣጣመ የወጪ በጀት እንዲኖር በማድረግ ቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸው የመንግስት ግዴታ ወጪዎችና ቀደም ሲል የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም፣ ለአፈር ማዳበሪያ ድጎማ፣ ለልማታዊ ሴፍትኔት፣ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ እና የወደሙ መሠረተ ልማቶችንና አገልግሎቶችን ወደ ቀድሞ ይዞታቸው ለመመለስ ቅድሚያ ትኩረት በማድረግና በኢኮኖሚ ማሻሻያው የተቀመጠውን የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚን የማስፈን ግብ ለማሳካት ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ እንደ ዕዳ ክፍያ የመሳሰሉ የመንግስት የግዴታ ወጪዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ በመምጣቸውና የመንግስትን የዕዳ ክፍያ ማዘግየት የማይቻል በመሆኑ ለዚህ የሚያስፈልገውን ወጪ በበጀት ማካተት የግድ ይላል፡፡ እንዲሁም የተጀመሩ የካፒታል ፕሮጀክቶችም ቢሆኑ የክፍያ ጊዜአቸውን በማሸጋሸግ የወጪ በጀት ቅነሳ በማድረግ ጭምር የተዘጋጀ የወጪ በጀት መሆኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡

የመደበኛ ወጪ በጀትን በሚመለከትም በየመ/ቤቱ እየተካሄደ ያለውን አዲሱን አደረጃጀት ከግምት ውስጥ በማስገባት እና የበጀት አጠቃቀም ቁጠባን መሠረት ያደረገና ውጤታማ እንዲሆን ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህም በሁለተኛው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ላይ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የሲቪል ሰርቭሱን የማስፈጸም አቅም የማጎልበት እና ጠንካራ ተቋማትን የመገንባት ተግባር በተጠናከረ ሁኔታ እንደሚካሄድ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

## ክቡር አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት

የ2017 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ረቂቅ በጀትን ለማዘጋጀት የተወሰዱ የገቢና የወጪ ታሳቢዎች ከላይ የተገለጹት ናቸው፡፡ ረቂቅ በጀቱን ለማዘጋጀት የተደረጉትን የማክሮ ኢኮኖሚ ታሳቢዎች ደግሞ እንደሚከተለው ለተከበረው ም/ቤት ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

የቀጣዩ የ2017 በጀት ዓመት በሀገሪቱ የተሻለ ሰላምና ሀገራዊ አንድነት ለማምጣት የሚደረጉት ጥረቶች ውጤታማ የሚሆንበት እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ይህም በተለይ እየተካሄደ ያለው ሀገራዊ ምክክር ለዚህ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህም

በተጨማሪ የገጠሙንን የማክሮ ኢኮኖሚ ተግዳሮቶች ለመፍታት ሁለተኛው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ተግባራዊ በመደረግ ላይ በመሆኑ በቀጣዩ በጀት ዓመት የተሻለ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ እንደሚኖር ግምት ተወስዷል፡፡

በዚህም መሠረት፣ ኢኮኖሚው ባለፉት ዓመታት ካጋጠሙት ጫናዎች በማገገም በያዝነው በ2016 በጀት ዓመት የ7.9 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ ተገምቷል፡፡ መንግስት የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት እያከናወነ ከሚገኛቸው ተግባራት በተጨማሪ፤ በበጀት ዓመቱ ለግብርና ተግባር አመቺ የሆነ የዝናብ ሽፋን በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች መኖሩ ዘርፉ ለኢኮኖሚ ዕድገት ጉልህ ድርሻ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም፣ በ2017 በጀት ዓመት ኢኮኖሚው የ8.4 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዝግብ ተተንብዮአል፡፡ ሁለተኛውን የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም ትግበራን ተከትሎ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረው ተሳትፎ እያደገ እንደሚሄድና ለዕድገቱም ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ታሳቢ ተደርጓል፡፡

የአጠቃላይ የፍጆታ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የዋጋ ዕድገት በበጀት አመቱ የመቀነስ አዝማሚያ እያሳየ ቢሆንም ለተወሰነ ጊዜ ባለሁለት አሃዝ ሆኖ እንደሚቀጥል ግምት ተወስዷል፡፡ ለዚህም ጥብቅ የገንዘብ እና የፊስካል ፖሊሲ እርምጃዎች ተግባራዊ እንደሚደረጉና አማካይ የዋጋ ንረት አሁን ግንቦት ወር መጨረሻ ካለበት 27.4 በመቶ በቀጣዩ በጀት ዓመት ወደ 12 በመቶ ዝቅ እንደሚል ታሳቢ ተደርጓል፡፡

የገቢ ዕቃዎች ዋጋ (value of imported goods) በ2016 በጀት ዓመት የአንድ (1) በመቶ ጭማሪ እንደሚኖረው የተገመተ ሲሆን በ2017 በጀት ዓመት ደግሞ የ9 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው ግምት ተወስዷል፡፡

## ክቡር አፈ ጉባኤ
## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት

ከላይ የተጠቀሱትን የማክሮ ኢኮኖሚ እና የፊስካል ፖሊሲ ታሳቢዎችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀውን እና ከባለበጀት መ/ቤቶች ጋር ሰፊ ውይይት ተደርጎበት በሚኒስትሮች ም/ቤት ተደግፎ የቀረበውን የ2017 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ረቂቅ በጀት እንደሚከተለው በዝርዝር አቀርባለሁ፡፡

በዚህም መሠረት በ2017 በጀት ዓመት ጠቅላላ የፌዴራል መንግሥት ገቢ የውጭ ርዳታን ጨምሮ ብር 612.7 ቢሊዮን እንደሚሆን ተገምቷል፡፡ በ2016 በጀት ዓመት ይሰበሰባል ተብሎ ከተገመተው

ጠቅላላ ገቢ አንጻር የ28.3 በመቶ ዕድገት አለው፡፡ ከዚህ ውስጥ ብር 502 ቢሊዮን ከታክስ ገቢ እንደሚሰበሰብ የተገመተ ሲሆን፤ ብር 61.6 ቢሊዮን ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች፣ ብር 7.3 ቢሊዮን ልማት አጋሮች በጀት ድጋፍ (sector budget support) እንዲሁም ብር 41.8 ቢሊዮን ከፕሮጀክቶች ዕርዳታ እንደሚገኝ የታቀደ ነው፡፡ በአጠቃላይ በ2017 በጀት ዓመት ከውጭ ዕርዳታ ይገኛል ተብሎ የሚጠበቀው ገንዘብ በ2016 በጀት ዓመት እንደሚገኝ ከተገመተው አንጻር የ59.3 በመቶ ጭማሪ አለው፡፡ ከሀገር ውስጥ ምንጮች ማለትም ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች እንደሚሰበሰብ የታቀደው ገቢ ብር 563.6 ቢሊዮን ነው፡፡ ይህም የአጠቃላይ ገቢውን 92 በመቶ ይሸፍናል፡፡ ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች ለመሰብሰብ ከታቀደው ብር 61.6 ቢሊዮን ውስጥ በአብዛኛው ከመንግስት የልማት ድርጅቶች ትርፍ ድርሻ የሚገኝ ነው፡፡ ቀሪው ከመንግስት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ሽያጭ እንዲሁም ከፈቃድና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎች የሚሰበሰብ ነው፡፡

## ክቡር አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት

የፌዴራል መንግሥት የ2017 በጀት ዓመት የወጪ በጀት ድልድል ከላይ የገለጽኩትን የወጪ የትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት በማድረግ የተደለደለ ነው፡፡ በዋናነትም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀውን የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍን ተከትሎ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አጠቃላይ የፌዴራል መንግስት የ2017 ጠቅላላ ወጪ በጀት ብር 971.2 ቢሊዮን ሲሆን፣ ይህም በ2016 በጀት ዓመት ከጸደቀው የወጪ በጀት አንጻር የ21.1 በመቶ ዕድገት አለው፡፡ ከዚህ የወጪ በጀት ውስጥ ብር 451.3 ቢሊዮን ለመደበኛ፣ ብር 283.2 ቢሊዮን ለካፒታል እንዲሁም ብር 236.7 ቢሊዮን ደግሞ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የበጀት ድጋፍ የተመደበ በጀት ነው፡፡ ከዚህ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ከተመደበው ጠቅላላ የበጀት ድጋፍ ውስጥ ብር 14 ቢሊዮን የሚሆነው የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማስፈጸሚያ ለክልሎች የተመደበ ድጋፍ ነው፡፡

ከዚህ ተደግፎ ከቀረበው ጠቅላላ የፌዴራል መንግስት የወጪ በጀት ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ለመደበኛ በጀት የተመደበው በጀት ነው፡፡ ይህም የጠቅላላ በጀቱን 46.5 በመቶ ድርሻ የያዘ ነው፡፡ ይህም በ2016 በጀት ዓመት ከተመደበው አንጻር የ21.9 በመቶ ዕድገት አለው፡፡ በጠቅላላ ለመደበኛ ወጪ የተያዘው የመደበኛ በጀት በኢኮኖሚ ጠቀሜታ ሲታይ ብር 127.2 ቢሊዮን (28.2 በመቶው) ለደመወዝ፣ ለአበልና ልዩ ልዩ ክፍያዎች የተመደበ ሲሆን፣ ቀሪው ብር 324.1 (71.8) ለስራ ማስኬጃ ተደግፎ የቀረበ ነው፡፡ ለሥራ ማስኬጃ የተመደበው ግን የ7.1 በመቶ ዕድገት ብቻ አለው፡፡ እንዲሁም ለመደበኛ ወጪ ከተደለደለው በጀት ለዕዳ ክፍያ የተያዘው በጀት ብር 139.3

ቢሊዮን ሲሆን፣ ይህም ለመደበኛ ከተመደበው ጠቅላላ ወጪ ውስጥ የ30.9 በመቶ ድርሻ ይዟል። ለዕዳ ክፍያ ከተያዘው በጀት ውስጥ 54.8 በመቶ ለሀገር ውስጥ ዕዳ ክፍያ እንዲሁም ቀሪ 45.2 በመቶ ደግሞ ለውጭ ሀገር ዕዳ ክፍያ የሚውል ነው።

በሌላ በኩል ለ2017 በጀት ዓመት ለፌዴራል መንግሥት ለካፒታል በጀት የተደለደለው ብር 283.2 ቢሊዮን ከጠቅላላ የወጪ በጀቱ የ29.2 በመቶ ድርሻ ሲኖረው፣ ለ2016 በጀት ዓመት ከተመደበው አንጻር የ39.2 በመቶ ዕድገት አለው። የካፒታል በጀት ወጪ አሸፋፈኑ ሲታይ ብር 216.5 ቢሊዮን ከትሬዠሪና ከመ/ቤቶች የውስጥ ገቢ፣ ብር 39.8 ቢሊዮን ከፕሮጀክት ርዳታ እና ብር 26.9 ቢሊዮን ከፕሮጀክት ብድር ለመሸፈን የተያዘ ነው። ለ2017 ከተመደበው ጠቅላላ የካፒታል በጀት ውስጥ ብር 187.1 ቢሊዮን (66.1 በመቶው) የተመደበው ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው ለመንገድ፣ ለትምህርት፣ ለግብርናና መስኖ፣ ለመጠጥ ውሀና ሳኒቴሽን፣ ለጤና እና ለገጠርና ከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔት ልማት ማስፈጸሚያ የተመደበ በጀት ነው። እንዲሁም በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ ንብረቶችንና አገልግሎት መስጫ ተቋማትን ወደ ነበሩበት ለመመለስና ለማቋቋም ለተጀመረው ፕሮጀክት ከመንግስት ትሬዠሪ ብር 20 ቢሊዮን ተደግፎ ቀርቧል።

እንዲሁም ባለፉት ዓመታት በተከሰቱ የውስጣዊ ግጭቶች ምክንያት በተጎዱ ክልሎች ውስጥ የመልሶ ግንባታ ሥራን ለማከናወን ጥረቶች እየተደረጉ ነው። በዚህም መሠረት የመልሶ ግንባታ ሥራውን ለማስተባበር በገንዘብ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ተቋቁሞ ሥራ የጀመረ ሲሆን በተመሳሳይ በአፋር፣ በአማራና በትግራይ ክልሎችም ጽ/ቤቶች ተቋቁመው ሥራ ጀምረዋል። ጽ/ቤቶቹ ባልተቋቋሙባቸው በቤኒሻንጉልና በኦሮሚያ ክልሎችም ተመሳሳይ ጽ/ቤቶችን ለማቋቋም አስፈላጊ የፋይናንስ ድጋፍ ተገኝቷል። እነዚህ የተቋቋሙ ጽ/ቤቶችም በፌዴራልም ሆነ በክልሎቹ የሚገኙ የዘርፍ ቢሮዎችንና ወረዳዎችን የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀትና ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ዕገዛ እያደረጉ ይገኛሉ። እንዲሁም፣ የመልሶ ግንባታውን ለማካሄድ ከፍተኛ ሀብት እንደሚያስፈልግ የተገመተ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ መንግስት ከመደበው በጀት በተጨማሪ የገንዘብ ሚኒስቴር የልማት አጋሮችን በማስተባበር ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ የሚሆን የሀብት ማሰባሰብ ሥራ እየተካሄደ ሲሆን፣ እስከ አሁን ድረስ 328 ሚሊዮን ዶላር ከዓለም ባንክ እና 47.1 ሚሊዮን ዩሮ ከጀርመን መንግስት ድጋፍ ማሰባሰብ ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ የግሉን ዘርፍ መልሶ ለማቋቋም የተለያዩ የመንግስት ተቋማትን በማስተባበር የተለየዩ የፖሊሲ ድጋፎች ተደርገዋል።

ለ2017 በጀት ዓመት ለክልል መንግሥታት የበጀት ድጋፍ ብር 236.7 ቢሊዮን ተደግፎ የቀረበ ነው። ከዚህ ለክልሎች ከተመደበው በጀት ውስጥ ብር 215.3 ቢሊዮን የሚሆነው የሚሸፈነው ከመንግስት

ግምጃ ቤት ነው። ቀሪው ከፕሮጀክት ርዳታና ብድር የሚሸፈን ነው። ከመንግሥት ግምጃ ቤት ለክልሎች ለ2017 የተመደበው በጀት ለ2016 ከተመደበው ጋር ሲነጻጸር የ5 በመቶ ጭማሪ አለው። በሌላ በኩል የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማስፈጸሚያ ለክልሎች ለ2017 በጀት ዓመት ብር 14 ቢሊዮን ተደልድሏል። ይህም ትራንስፎርሜሽንን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ለስራ ዕድል ፈጠራ እና በክልሎች ለሚካሄዱ ለአነስተኛ እና መካከለኛ መስኖ ልማት ካፒታል ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚውል ነው።

## ክቡር አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት

ከዚህ በላይ በዝርዝር ለማቅረብ እንደሞከርኩት በ2017 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ከሀገር ውስጥ የገቢ ምንጮች እንዲሁም ከውጭ ርዳታ በድምሩ ብር 612.7 ቢሊዮን ገቢ እንደሚሰበሰብ በዕቅድ ተይዟል። እንዲሁም ለመደበኛ፣ ለካፒታል እና ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የበጀት ድጋፍና የዘላቂ የልማት ግቦች ማጠናከሪያ ወጪ ጠቅላላ ብር 971.2 ቢሊዮን በጀት ተደግፎ ቀርቧል። በመሆኑም በቀጣዩ የበጀት ዓመት የበጀት ጉድለቱ ባለፉት ዓመታት ከነበረው አንጻር ትርጉም ባለው መጠን እንዲቀንስ የተደረገ ሲሆን ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 2.1 በመቶ ነው። ይህም የበጀት ጉድለት ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር በሚወሰድ ብድር ለመሸፈን ታቅዷል። ይህ የበጀት ጉድለትም መንግስት የተረጋጋ ኢኮኖሚ ለማስፈን ካስቀመጠው ግብ ጋር የተጣጣመ ነው። የሀገር ውስጥ ብድር አወሳሰዱም የዋጋ ንረትን በማያስከትሉ የብድር መሳሪያዎች ማለትም የመንግስት ግምጃ ቤት ሰነዶችን እና የመካከለኛ ዘመን ቦንዶችን በመሸጥ ለመሸፈን የታቀደ ነው።

ለ2017 ተደግፎ የቀረበው ይህ ረቂቅ የፌዴራል መንግስት በጀት ካለፉት ዓመታት በጀት ጋር ሲነጻጸር መጠነኛ ጭማሪ ቢኖረውም ከልማት ፍላጎታችን አንጻር በቂ ነው ለማለት አዳጋች ነው። ሆኖም የማክሮ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት እና የያዝናቸውን የልማት ግቦችን ለማሳካት ሚናው ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ባለበጀት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት ለታለመለት ዓላማ በቁጠባና በላቀ ውጤታማነት ጥቅም ላይ ማዋል እንዳለባቸው ከፍተኛ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል። በተጨማሪም የሚጸድቀውን በጀት የመንግስትን የፋይናንስ፣ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ህጎችን እና ሥርዓቶችን ተከትለው ስራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል። ይህንንም ለማረጋገጥ የክትትልና የቁጥጥር ስራውን በማጠናከር ከሥርዓቱ ውጭ ለሚደረግ የበጀት አጠቃቀም ተጠያቂነትን የማረጋገጥ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

በአጠቃላይ ይህ የ2017 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት በጀት በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን እየተመኘሁ፣ የበጀት ዝግጅቱ የተሳካ እንዲሆን የበጀት ጥያቄያቸውን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳና በተዘጋጀው የበጀት ሥርዓት መሰረት ላቀረቡ አስፈጻሚ አካላት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ረቂቅ በጀቱ ላይ ሰፊ ውይይት በማካሄድ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት ለዚህ ምክር ቤት እንዲቀርብ በማድረጉ፣ እንዲሁም የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት የበጀት መረጃዎችን ለሕዝብ በማስተላለፍ ላደረጉት አስተዋጽኦ በመ/ቤቴ ስም ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም ይህን ተደግፎ የቀረበውን የ2017 ፕሮግራም በጀት የተከበረው ምክር ቤት እንዲያጸድቀው በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

## አመሰግናለሁ፡፡